# የወያኔ እጆች ሲዘረጉ ሕዝብ ተቋሞቹን ለመጠበቅ መዘጋጀት አለበት

ዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጥፋት፡ የመከራና የግፍ አገዛዙን ከዘረጋበት 20 ዓመታት ወዲህ ኢትዮጰያዊ ታሪካችንን እያጠፋ፡ ተቋሞችን እያፈራረሰ፡ ኢትዮጵያዊነትን በማንኳሰስና በማዋረድ ብሔራዊ ክብራችንን እያስደፈረ፡ ሕዝብን በመከፋፈልና በማጋጨት የስልጣንን ዘመኑን እያረዘመ ሲሄድ፤ ሊገድለው፡ ሊያስረውና ያፈለገውን ሊያደርግ ያልቻለው በውጭ ነዋሪ የሆነውን ኢትዮጵያዊ ነው።

በተለይም በምርጫ 2005 አካባቢና ከዚያም በሁዋላም ወያኔ የሕዝብን ድምጽ ዘርፎና ከ200 በላይ ሰላማዊ ዜጎችን ጨፍጭፎና ከ30000 በላይ ወጣቶችን በየእስር ካምፑ አጉሮ በሚያሰቃየበት ጊዜ ሌት ተቀን፡ ክረምት ከበጋ፡ ሳይል የተቃውሞ ድምጹን ሲያሰማ የነበረውን ዲያስፖራ ለመከፋፈልና ለማዳከም ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ በመመደብና 52 ገጽ ማንዋል በየኤምባሲዎቹ ልኮ ተቃውሞውን ለማዳከም መስራቱን የምናስታውሰው ነገር ነው።

በአሜሪካ፣ በካናዳ፡ በአውሮፓ፡በአፍሪካ እና በአውሰትራሊያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተቋሞችን፡ ማለትም የሃይማኖት ተቋሞችን፡ የኢትዮጵያ ማህበራትን ሌላው ቀርቶ መረዳጃ ማህበሮችና እድሮችን ሰዎቹን አስርጎ በማስገባት ብጥብጥ በመፍጠር እያከፋፈለና እየበታተነ ይገኛል። በበዙ አገሮች ሕዝብ በየፍርድ ቤቱ ሲጓተትና ሲጨቃጨቅ የተቃውሞ ድምጹን ለማሰማት አቅምና ጊዜ እያጣ የዲያስፖራው ትግል ተዳክሞ ይገኛል።

በካናዳ የወያኔ ኤምባሲም በሌላው አገር የተደረገውን ለማድረግ ብዙ አድርጓል። የሕዝብ ሰፈራ ፕሮግራም የያዘ ይመስል የወያኔ ካድሬዎቹን በቶሮንቶና በሌሎች ትላልቅ ከተሞች በትምህርት ሰበብ፡  ጎረምሳ ካድሬዎቹን በሃይማኖት ሽፋን ስም ዘርፋፋ ቀሚስ እያለበሰ በብዛት ማስገባት ከጀመረ ሰነባብቷል። የከተማውን መንገዶች ያጣበቡት ልጆቻቸው ውድ ትምህርት ቤት በገንዘብ እየተከፈለ ውድ መኪና እየነዱ በቆየው ነዋሪ ላይ እየዘነጡ ማንነታቸውን ማሳየት አዲስ ነገር መሆኑ ቀርቷል።በቅርቡ ደግሞ የወያኔ ኤምባሲ ከኦታዋ የጥፋት ተልዕኮውን በመዘርጋት በቶሮንቶ ከተማ የቆንስላ ቢሮ በመክፈት ላይ ሲገኝ፡ “በካናዳ የኢትዮጵያ ማህበር ካውንስል” የሚል የወያኔ ቡድን ከዚሁ ከቆንስላ ቢሮ ጋር ተዳብሎ እንደሚሰራም እየሰማን ነው።

የወያኔ ኤምባሲ ቢሮ መክፈቱ መብቱ ስለሆነ ማንም አይከለክለውም። መታወቅና መጠንቀቅ የሚያስፈልገው ግን ከጀርባ ሊሰራ ያሰበው የጥፋት ተልዕኮ በወቅቱ መጋለጥ ስላለበት ያንን ለቶሮንቶ ነዋሪና በሌሎችም ክፍለሀገሮች ያሉ በጊዜ እንዲጠነቀቁ ለማድረግ ነው። ዋናው ዓላማቸው አንጋፋውና ከ25 ዓመት በላይ እድሜ ያለውን የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢን ለመቆጣጠር ወይም ለማፍረስ ነው!! ወገን አንድ የኢትዮጵያውያን መሰባሰቢያ ተቋም ቢኖረን በእርሱ እየመጡብን ነውና የማህበሩ አባላትና ደጋፊዎች የቦርድ አባላትና ሰራተኞች ሁሉ በአንድነትና በጋራ ሆነን ቤታችንን  በማዳን በኩል በንቃት ለመጠበቅ ያላሰለሰ ርብርቦሽ በማድረግ ብቻ ነው። ይህንን ማህበር አሁን ያለበት ደረጃ ለማድረስ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ብዙ የደከሙበትና መስዋዕትነት የከፈሉበት ነው!!

ሕጋዊ ማህበራችንን ለማዳን ስንጮህ ድምጻችንን ነጥቀው ተመሳሳይ የሀሰት ጩኸት በማሰማት ግራ እንዳያጋቡን ብልህና አስተዋይ መሆን አለብን። ማህበሩን አፍርሰው በየአካባቢው የጎሳ ማህበራትን ለማቋቋም እየሰሩ መሆኑንም የአደባባይ ምስጢር ነው። በመሀከላችንም ንፋስ እንዳይገባ መጠበቅና መከላከልም አለብን።

የኢትዮጵያን ማህበርንና ተቋማትን ከወያኔ ሰርጎ ገቦች እንጠብቅ!

ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ

ኖቬምበር 2010